**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት**

**ትእዛዝ**

**(በ3/19/20 የተሻሻለው)**

በማርች 18፣ 2020 በተላለፈው ትእዛዝ መሰረት፣ ጆይንት ኮሚቲ ኦን ጁዲሽያል አድሚኒስትሬሽን (የፍትህ አስተዳደር የጋራ ኮሚቴ) አሁን ባለው የፍትሕ አስቸኳይ ጊዜና ለፍትህ አስተዳደርም የተሻለ ስለሆነ በዲ.ሲ. ኮድ እና የሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግ እና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ታግደው፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ቆመው (ቶል ተደርገው) እና ተራዝመው የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ለማራዘም የሚያስችሉ ትእዛዞች ለማድረግ ለዋና (ቺፍ) ዳኛ ስልጣን ሰጥቷል።

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤት፣ በዋና (ቺፍ) ዳኛ ትእዛዝ፣ ከኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ጋር በተያያዘ ላሉት ስጋቶች ለመቅረፍ በአሰራሩ ማስተካከያዎች እያደረገ ይገኛል። ፍርድ ቤቱ እንደየ ሁኔታዎቹ ተጨማሪ ማስተካከያዎች ያደርጋል።

የጉዳይ አይነቱ ከታች ያልተገለጸ እስከሆነ ድረስ፣ ከመይ 15፣ 2020 በፊት ተቀጥረው የነበሩ ቅድሚያ-የማይሰጣቸው (ናን-ፕራዮሪቲ) ጉዳዮች ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል፣ አዲስ ቀነ ቀጠሮ ይያዝላቸዋል፣ አስቸኳይ ጉዳዮች ፍርድ ቤቱ ይዞላቸው ባለ ቀጠሮ ይቀጥላሉ፣ ከታች እንደተቀመጠውም ይሰማሉ።

የኮቪድ-19 ምልክቶች ያሉት ማንኛውም ጠበቃ ወይም ሰው ወደ ፍርድ ቤት እንዳይገባ ታዟል። https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/about/symptoms.html ይመልከቱ

ማንኛውም ከነዚህ ለውጦች እፎይታ (ረሊፍ) መጠየቅ የሚፈልግ አካል በተገቢው ፍርድ ቤት አቤቱታ ፋይል በማድረግ እፎይታ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።

**ፋይል ማድረግ (ፋይሊንግ)፡**

ፋይል ለሚደረጉ ማመልከቻዎች (ፕሊዲንግስ)፣ አቤቱታዎችና አዳዲስ ጉዳዮች ለመቀበል፣ ሁሉም ክፍሎችና የቤተሰብ ፍርድ ቤት፣ በተወሰኑ ሰራተኞች ክፍት ይሆናሉ። በኤሌክትሮኒክ መንገድ ፋይል ማድረጉ ይቀጥላል።

የሚከተሉት ሂደቶች (ፕሮሲጀርስ) እስከ መይ 15፣ 2020 ድረስ ተግባራዊ ይሆናሉ፡

**ፋይል የሚደረግበት የጊዜ ገደብ ማገድ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ማቆም (ቶሊንግ)፣ እና ማራዘም፡**

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር ከመይ 15፣ 2020 በፊት እንዲፈጸሙ በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸውና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች፣ ክስ ፋይል ለማድረግ የሚሰጠው ጊዜ (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽንስ) ጭምር፣ የአስቸኳይ ጊዜ ተግባር ላይ እስካለ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ። እነዚህ የጊዜ ገደቦች እንደ ሁኔታው ለተጨማሪ ጊዜ ሊታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ሊቆሙ (ቶው ሊደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ሊራዘሙ ይችላሉ።

**የፍርድ ቤት ስራዎች፡**

ፍርድ ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች ብቻ ይሰማል፡

- የከባድ ወንጀል (ፌለኒ) መቅረቦች (ፕረዘንትመንትስ)፣ እና የቀላል ወንጀል (ሚስደሚነር) ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት መቅረቦች (አረይንመንትስ)። ይህ በመጥሪያ (ሳይቴሽን) ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት መቅረቦች (አረይንመንትስ) አያጠቃልልም፣
- የወጣት ጥፋተኞች (ጁቨናይል) የመጀመሪያ ቀጠሮዎች (ኢኒሻል ሂሪንግስ) እና መልስ ሰጪ ፍርድ ቤት መቅረብ በነበረበት ጊዜ ባለመቅረቡ ትእዛዝ እንዲሰጥ ለመጠየቅ (ሪት ኦፍ ሀቤስ ኮርፐስ) የሚቀርቡ አቤቱታዎች፣
- የጉዳትና ቸልተኝነት (አቢዩዝ ኤንድ ነግለክት) ጉዳዮች የማስወገድ (ሪሙቫል) እና የመጀመሪያ ቀጠሮዎች (ኢኒሻል ሂሪንግስ)፣ እና
- አስቸኳይ ጉዳዮች ብቻ።

ጉዳዮች የሚሰሙ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ናቸው፡

- C-10፡ በወንጀል ተከሶ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት መቅረቦች (አረይንመንትስ) እና የከባድ ወንጀል (ፌለኒ) መቅረቦች (ፕረዘንትመንትስ)
- JM-15፡ የቤተሰብ ፍርድ ቤት አስቸኳይ ጉዳዮች፣ የቸልተኝነት የመጀመሪያ ቀጠሮዎች (ኢኒሻል ሂሪንግስ)፣ እና የወጣት ጥፋተኞች (ጁቨናይል) የመጀመሪያ ቀጠሮዎች (ኢኒሻል ሂሪንግስ)
- 115: የወንጀል ክፍል እና የቤት ውስጥ ብጥብጥ አስቸኳይ ጉዳዮች- ይህ የቲ.ፒ.ኦ.ዎች አስቸኳይ ጉዳዮች አያካትትም፣ እነዚህ ጊዳዮች በዌብ ኤክስ (Web Ex) ይሰማሉ፣ ከታች ያለውን ይመልከቱ
- 516፡ የፍትሐብሔርና፣ የኑዛዜን ወይም ውርስን ህጋዊነት ማረጋገጥ (ፕሮቤት) እና የግብር (ታክስ) ክፍሎች አስቸኳይ ጉዳዮች (ጃጅ ኢን ቻምበርስ)

ሁሉም ሌሎች ጉዳዮች ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል፣ አካላቱ መቅረብ የለባቸውም፣ ፍርድ ቤቱ አዲሱ ቀነ ቀጠሮ ለአካላቱ ያሳውቃል።

<u>ተጨማሪ ጉዳዮች፡</u>

- ሁሉም በሂደት ያሉ በጁሪ እየታዩ ያሉ ክርክሮች (ጁሪ ትራያልስ) ተይዞላቸው ባለ ቀጠሮ ይቀጥላሉ።
- ፍርድ ቤቱ በሁሉም ክፍሎች ያለ ፍርድ ቤት ቀጠሮ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ለሚችሉ አቤቱታዎችና ጉዳዮች ውሳኔ መስጠቱ ይቀጥላል።
- የፋይል ማድረጊያ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች መክፈል አንችልም እና በነጻ ይደረግልን ብለው የሚጠይቁ ማመልከቻዎች አካላት ፋይል ማድረግ ይችላሉ፣ ፍርድ ቤቱም ውሳኔ ይሰጥባቸዋል።
- ፍርድ ቤቱ በግለሰቦች የሚደረግ በፍርድ ቤት የታዘዙ ክፍያዎች ይቀበላል፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ መደረግ የሚችሉት የወንጀል ጉዳዮች ክፍያዎች፣ ከቦንድ ክፍያ በስተቀር፣ ብቻ ናቸው። በተጨማሪ፣ ማንኛውም በመከላከያ ትእዛዝ (ፕሮቴክቲቭ ኦርደር) መሰረት ለፍርድ ቤት ክፍያ እንዲያደርግ ታዞ የነበረ ተከራይ በዙሁ አስቸኳይ ጊዜ ታግዷል። ተከራዮች ክፍያው በቀጥታ ለአከራዮች ያድርጉ። ክፍያ በቀጥታ መቀበሉ፣ አከራይ እርምጃ ለመውሰድ ለሚያደርገው የፍርድ ቤት ሂደት አይጎዳም። የማህበረሰብ አስቸኳይ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ የመከላከያ ትእዛዝ (ፕሮቴክቲቭ ኦርደር) ተጥሷል በማለት አከራይ ማእቀቦች እንዲጣሉ ቢፈልግ፣ ከሌሎች ተገቢ ሁኔታዎች በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ከማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባል።
- ሁሉም በመይ 15፣ 2020 ወይም ከዛ በፊት መከናወን የነበረባቸው ተከራዮችን ከተከራዩበት ቤት፣ ቤታቸው በሀራጅ የተወሰዱባቸውን ደግሞ ከነበራቸው ቤት ማስወጣት (ኢቪክሽንስ) ሳይተገበሩ ይቆያሉ።
- የወንጀለኛ ዝውውር (ኤክስትራዲሽን) ጉዳዮች ተይዞላቸው ባለ ቀጠሮ ይቀጥላሉ።
- በግራንድ ጁሪ የተመለሱ ክሶች (ኢንዳይትመንትስ) እንደ ቀረቡት ይቀበላሉ፣ ሁሉም ግራንድ ጁሪ ፊት መቅረብ በተመለከተ ያሉ ጉዳዮች እንደ ቀረቡ ተደርገው ይቆጠራሉ።
- የቅድመ-ክርክርና የፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ) ቀጠሮዎች እና ቦንድ መመዘኛ ወይም ቅድመ ሁኔታ መተውያ አቤቱታዎች መቀጠል ይችላሉ፣ ተገቢ ሲሆን በወንጀል ክፍል የአደጋ ጊዜ ዳኛ (ኢመርጀንሲ ጃጅ) ይታያሉ።

- ማንኛቸውም ተግባር ላይ ያሉ ጊዚያዊ የመከላከያ ትእዛዞችና የፍትሐብሔር መከላከያ ትእዛዞች ተግባራዊነታቸው ይቀጥላል፣ እስከ መይ 15፣ 2020 ወይም ወደሚቀጥለው ፍርድ ቤቱ የሚመድበው ቀጠሮ ይራዘማሉ።
- የጊዝያዊ መከላከያ ትእዛዞች ጥያቄዎች፣ በአስቸኳይ ጊዝያዊ መከላከያ ትእዛዞች ሂደት (ኢመርጀንሲ ቴምፖራሪ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ ፕሮሰስ (ኢ.ቲ.ፒ.አ.) በኩል ይገኛሉ። በዚህ በአስቸኳይ ጊዜ የፍርድ ቤት ስራ ሁኔታ የኢ.ቲ.ፒ.አ. ሂደት አስቸኳይ አደጋ ላላቸው ሁኔታዎች በቀን በማንኛውም ሰአት ማግኘት ይቻላል። በአስቸኳይ አደጋ ውስጥ ካሉና ፖሊስ (911) ወይም በ(800) 407-5048 ለዲ.ሲ. ሴፍ ክሪቲካል ሪስፖንስ ቲም ከደወሉ ለአስቸኳይ ጊዝያዊ መከላከያ ትእዛዝ (ኢመርጀንሲ ቴምፖራሪ ፕሮቴክሽን ኦርደር) ብቁ መሆናቸው ለመወሰን ወደ ኢ.ቲ.ፒ.አ. ይመራሉ።
- የፍትሐብሔር የመከላከያ ትእዛዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደር) በwww.probono.net/dccourts በመተቀም በአስቸኳይ ፋይል ማድረግ ይቻላል። ቅጾቹ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ሞልተው ማስረከብ ይችላሉ። ቅጾቹን ሞልተው ካስረከቡ በኋላ እባክዎ ፋይል ማድረጉ ለመቀጠል የክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮ በስልክ ቁጥር (202) 879-0157፣ ወይም በኢመይል አድራሻ domesticviolencemanagement@dcsc.gov ያግኙ። በተጨማሪ፣ የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል ቅጾች በዲ.ሲ. ፍርድ ቤት ድረገጽ http://www.dccourts.gov/services/forms?title=&combine ማግኘት ይችላሉ፣ እና ቅጾቹን ከሞሉ በኋላ ወደ domesticviolencemanagement@dcsc.gov ይላኩ። በድረገጹ የሌለ ቅጽ ካለ እባክዎ ለተጨማሪ ድጋፍ ለdomesticviolencemanagement@dcsc.gov ኢመይል ይላኩ።
- የጋብቻ ቢሮ (መርየጅ ቢሮ) በዚህ ጊዜ የጋብቻ ምስክር ወረቀት አይሰጥም። አስቀድሞ ቀጠሮ የተያዘባቸው የጋብቻ ስነ ስርአቶች ተይዞላቸው ባለ ቀጠሮ አይቀጥሉም። ስነ ስርአትዎ ወደ ሌላ ቀን መቀየር ከፈለጉ እባክዎ የጋብቻ ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1212 ያግኙ።